# <u>ግንቦት 7--የኤርትራ ቱሪስት ወይስ ተጋደላይ ?</u>

ተመስገን ልመንህ

ኤፍሬም ማዴቦ (ሌጅቦ ይሉታል አንዳንዶች) ከኤርትራ የሚያይዘው ብዙ ነገር አለው ። በዚያ መቆየቱና ጋብቻው ብቻ ሳይሆን በሌላም። በቀይ ሽብር ጊዜም ብዙ ወጣቶችን በመግደልና በማስገደል ወንጀል ተፈላጊ ነው የሚሉም አሉ ። ይህን ለጊዜው እንተወውና አቶ ኤፍሬም በፖለቲካው መስክ እንደ ግንቦት 7 መሪ ግን የዚህን ድርጅት ንዝህላልነትና ቅጥረኛነትን ወግ ማዕረግ ብሎ የተላበሰ ነው ።

በረሀ ገባ፤ ትግሉን ተቀላቀለ፤ኤርትራ ሄደ ተብለን ወር ሳያልፍ --አስመራ መግባት ትግል መቀላቀል ነው ወይስ ድንበርን አልፎ፤ነፍጥ አነግቦ ከወያኔ መፋለም?--- የአቅሚቲ ወረቀቱን ጫጭሮ እነሆ ሲለን(ከአርበኛች መንደር ይለዋል) ጉድ ማለት ተገደናል ። የግንቦት 7 መሪዎችና ኢሳት የሚባለው ተቋም ቦርጫሞች ከአሁን ወዲያ አያስገርሙንም ስንል ሌላ ደረጃ ዝቅጠት ይዘው ይመጡና ጉድ ያሰኙናል ። ኤፍሬም በረሀ ገቡ የተባሉት ብርሃኑና ነአምን አስመራ እየተንፈላሰሱና ጥላሁንን እያዳመጡ መሆናቸውን ይነግረናል። ሐሬናም ጉልችም የማይቻል በረሓ ሆነባቸው ማለት ነው ። ኤፍሬም በጻፈው ጽሁፍ ዋናው ተልእኮው ለሻእቢያ የቱሪስት ቢሮ (አላቸው ይሆን ይህ ተቋም? ማን ጎብኚ ወደ መከራ ምድር ሊመጣ፤ ይሽሻል እንጂ!) የሆነ ይመስል ስለ ገጠር ኤርትራ በኤኮኖሚ እንቅስቃሴ መናጥ ወዘተ ያቀርባል ። አሳፋሪዎቹ የኢሳት ቦርጩዎች አምባገነኑ ፊት ቀርበው ያሳዩትን ዝቅተኛነት ያንጸባርቃል ። በዚህ በዚያ በምጽዋ ሳይቀር ተዟዙሮ መጎብኘቱን ኤፍሬም ያወጋናል ። ሁሉም ነገር ምስጢር ነው በዚች ምድር ሲለን ይቆይና የእያንዳንዱን የጦርና ማሰልጠኛ ሰፈር ከነኮረንኮች ማጠፊያውና የፈጀውን ደቂቃ ጨምሮ ይነግረናል ።ወያኔ ካላወቀው ለኤፍሬም ይቀንየሌ' ማለቱ ይጠበቃል ። ዞሮ ዞሮም ኡም ሀጀርም ደረስኩ ብሎ ግን ድንበር አቋርጬ ኢትዮጵያ ገባሁ አይለንም ። ገሰገሰ የተባለውና አሁን ደግሞ ሳንጃን (ላይ አርማጨሆ) ያዘ የተባለው የብርሀኑ የውሸት ጦር ራቀው እንበል ?

እድሜ ለኤፍሬም ጦር የሚባለው እዚያው ሐረና ሰፍሮ እንዳለ ተነግሮናል ። በሻዕቢያ አቀነባባሪነት ሰሞኑን ሊታወጅ የተዘጋጀው "ግንባርም" እንዳለ ብርሃኑ ያለውን ዳግም ኤፍሬም አቅርቦታል ። ታጋዩ"በየተሬውና ድንኳኑ" ተከፋፍሎ እንዳለም ተገልጿል ። ሜዳ ገቡ? እነማን ! ከዚህ ቀደም ተብሎና ተጋልጦ እንደነበረው ግንቦት7-አርበኛች ከሻእቢያ ንኡስ ተለጣፊዎች-ኩልኩልቶች (ሲአን፤ ቤኒ ሻንጉል፤ ሻዕቢያ ከፈቀደ ዴምህት፤ የአፋር ቡድን፤አንድ የኦነግ ተገንጣይ ቡድን) ጋር የተባለውን ፋይዳ ቢስ ግንባር ያውጃል ። የፈረደበት በውጭ ነዋሪ ዜጋ ደግሞ በጀሮው ላይ ተኝቷልና ከገንዘቡ ይለያያል ። የነ ብርሃኑ ኪስም ይዳብራል ። ሌላ ውጤት የለም ። ብርሃኑን በጎጥ ስሜት ሆነ ተላላ ሆነው ጆሮ የሰጡት ውስጥ ውስጡን እያፈሩ መሆናቸው ግልጽ ነው ። ኪሳራ መጥቷልና አማራ የለም ባዩን ፕሮፌሰር ከወደ አዲስ አበባ ወደ አሜሪካ አምጥተው ሊነጋግሩበት ተደረጅተዋል ። የመላኩ ተፈራ ዘፋኝና የአላሙዲም ቅሪላ ሆኖ ለዓመታት የቆየው ታማኝ በየነም በበቂ ደሞዝ በኢሳት ላይ ተሹሞ የብርሃኑን ውጉዝ ሻቢያዊ ዓላማ ከግብ ለማድረስ እየተሯሯጠ ነው ።

ጋዜጠኛ ደምስ ያለውን የማጭበርበርና የሻዕቢያ ሴራ በበቂ በማጋለጡ ግንቦቶቹ ቅጥረኞቻቸውን አሰማርተውበታል ። ፈሩ መሰል ሌሎቹ የግንቦት 7ን ሴራ ማጋለጥ የጀመሩት ዝምታን መርጠዋል ። ይቺ ብቻ ናት እንዴ ትግል? ዝገርም ይላል የሀገሬ ሰው። ጋዜጠኛ ደምስ ዘግይቶ ይፈንዳ አይፈንዳ አይደለም ጥያቄው-- የጻፈው ሀቅ ነው ወይስ ውሸት የሚለው ነው ቁም ነገሩ ። በይነገር ዓለሙ ሽፋን ስም የሚጽፈው ፈሪም ማንነቱ ለብዙዎች ምስጢር ያልሆነው የቆሻሻ ታሪክ ባለቤት ብርሃኑን በማዳነቅና ሌሎችንም በአያሌው በመስደብ ደምስንም ሌሎችንም አፋቸውን ሊዘጋ ቢጥርም አልተሳካለትም ፡፡ እውነት ለሁሌም የሚደበቅ ነገር አይደለምና ፡፡ ሻዕቢያ ጋ መሄድ አይደለም ጥያቄው--ቁም ነገሩ ሻእቢያ ማንም በጸረ ወያኔ እንቅስቃሴ በቁርጠኛነት እንዲሰማራ አለመፈለጉ ነው ። ከብርሃኑ በፊት ሟቹ ተስፋዬ ጌታቸው በዚያው ነበር። የት ደረሰ? በራሱ በሻዕቢያ ተገደለ እንጂ ።ይረዳናል ብለው ያመኑና ወደ ሐሬና የሄዱ ሕይውታቸውን በሻዕቢያ እጅ አጥተዋል

። ብዙዎች ታስረውና ተገርፈው እየማቀቁ ናቸው ። በአጭሩ ወያኔን ከሻዕቢያ ጋር ወግኖ መዋጋትና መጣል እይቻልም ነው ። እንደ ኤፍሬም ኤርትራን መንብኘትና የድሮን ትዝታ ማቀፍ ግን የሚቻል ነው ። ነጻ አወጣናት የሚሉት በየኮንቴኔይሩ ታሽገው ስቃይ የሚቀበሉባትን ኢርትራ እያደነቁ መንብኘት ይቻላል ። ህሊናን መግደል ብቻ ነው የሚያስፈልገው ፡፤ እንደ ግንቦት 7 አሳፋሪ መሪዎች ።

ተመስገን ልመንህ